የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

*ከኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነትና*

*ከኢትዮጵያ ሕሪዝብ ብሔራዊ ፓርቲ*

*<u>የይድረስ ጥሪ፡-</u>*

ሚያዝያ 28 ቀን 2012 ዓ ም

*“ለወገን ደራሽ ወገን ነው”ይላሉ አባቶች ሲተርቱ አባባሉ ዘመን የማይለውጠው ጊዜ የማይሽረው ነው። አባብሉን ዘመን እንዳልሻረው ሁሉ ተግባሩም ዛሬ እንደማይሻርው እሙን ነው። ወደ ዋናው ቁም ነገር ስንመለስ ዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በትግሬ ወያኔ እየተፈጸመ ያለው መዓትእጅግ በጣም ዘግናኝ ነው። በተለይ በአሁኑ ሠዓት ከቤኒሻንጉል በተፈናቀሉ የአማራ ዜጎቻችን ላይ የሚደርሰው ግፍና መከራ ለኅሊና የሚሰቀጥጥ ነው። እነዚህ ዜጎቻችን ለዘመናት ከኖሩበት ከበኒሻንጉልና ከምዕራብ ኢትዮጵያ የተፈናቀሉት በትግሬ ወያኔ ካድሬዎች እንጂ በነዋሪው ሕዝብ ጥላቻ እንዳልሆነ ሕዝቡም ሆነ ተፈናቃዮቹ በይፋ ይናገርሉ። እነዚህ የአማራ ተወላጅ ዜጎቻችን ከጥንት ጀምረው ከአከባቢው ሕዝብ ጋር ተጋብተውና ተዋልደው ለዘማናት አብረው የኖሩ ከፊሎቹ በለርስትና ባለድርጅቶችም እንደ ነበሩ የታወቀ ነው።*

*እነዚህ ዜጎቻችን ቀደም ብሎ በነበረው በንጉሳዊው አስተዳደርም ሆነ በደርግ አስተዳደር ጊዜ የዜግነት መብታቸው ተከብሮ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በነፃነት ይኖሩ እንደ ታወቃል። ዛሬ የወለጋ ሕዝብ ለእነዚህ ተፈናቃዮች የዕለት ጉርሻ እንዳይሰጣቸው በወያኔ*

*ጉዳይ ወታዳሮች እየተከለከሉ ነው። የአማራው ሕዝባችን ከሦላሳ በላይ ዜጎቻችን*

*ተጨፍጭፈው ሲገደሉ ፤ በሕይወት ተርፈው አማራ ተብሎ የተከለለው*

*ኦከባቢ የደረሱ እርጉዞችና አቅመ ደካሞች ሳይቀሩ በልመና ላይ የተሰማሩት በምሬት*

*እየገለጹ ናቸ።*

*እነዚያ በሕይወት ተርፈው በልመና ላይ የተሰማሩ ከሕዝብ ተመጽውተው ሕይወታቸውን*

*እንዳያሰነብቱ የውያኔ ወታደሮች ወደ መጡበት እንዲመለሱ በሚል ሰበብ እየልቀሙ በእሥርቤቶች እያጎሩዋቸው ነው።*

*የትግሬ ወያኔዎች እቅድ ከመከራው ተርፈው ከወገን የተቀላቀሉትን ተመልሰው ሄደው እንዲጨፈጨፉ ለማድረግ እንጂ አዝነውላቸው እንዳልሆነ ተጎጂዎቹ ተገዝበው*

*የይድረሱልኝ ተማጽኖ እያሰሙ ናቸው። ሰባዊነት ተሰምቷቸው የዕለት ጉርስ*

*የሚሰጧቸውን ወገኖች እየደበደቧቸው ነው።*

*የኦሮሞ ሕዝባችን በሱማሌ ታጣቂዎ ሲፈናቀል አብሮ የተፈናቀለው የአማራ ሕዝባችን*

*ምንም ልዩነት ሣይደረግበት ከሮሞ ወገኑ ጋር እይተረዳ ነው።*

***የተከበራችሁ ወገኖቻችን !!!***

*ለወገን ደራሽ ወገን ስለሆነ ይህ ከዉርደት የወደቀውን ሕዝባችንን ለመታደግ ሚዲያዎች*

*ጥሪያችንን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲታስተላልፉልን እየጠየቅን ፤ ዛሬም ሆነ*

*ትላንት ኢትዮጵያዊ በትውልድ ቂዬው ስደተኛ እንዲሆን፣ ከዚያም አልፎ እንዲገደል ያደረጉ ያሉት በተለይ በአማራው ሕዝብ ላይ እንደ በበረከት ሰሞዖንና በከሃዲው በአዲሱ*

*ለገሠ እንደሆኑ የሚያጣው ኢትዮጵያዊ የለም። እነዚህን ከሃዲግ ለሰቦች ታሪክና ትውልድ*

*እንደሚፋረዳቸው ማንም ኢትዮጵያዊ የሚጠባበቀው የወደፊት ሐቅ ነው።*

| | |
|---|---|
| ኢሕብፓ<br>EPNP<br>የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ<br>ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY | ኦሕንኢስ<br>OPMEU |

EPNP.INFO

EPNP
የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY



EPNP

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY